# ስለ FY26 ካፒታል በጀት እና 2025-30 የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም ማሻሻያዎችን በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ

**ኦክቶበር 23, 2024**

በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሱፐርቴንደንት 2026 ዓ.ም ካፒታል በጀት እና 2025-2030 የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም ባጀት ማሻሻያዎችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ አቅርበዋል።
Superintendent's Recommended FY 2026 Capital Budget and Amendments to the FY 2025-2030 Capital Improvements Program to the Montgomery County Board of Education.

ሱፐርኢንቴንደንት ዶ/ር ቶማስ ቴለር በድርጅቱ ውስጥ በሁሉም ደረጃዎች ያሉ ሰራተኞች ተገቢውን የፋይናንስ ፕሮቶኮሎችን እና ልምዶችን መጠበቅና ማክበር እንደሚጠበቅባቸው ገልፀዋል። ስለ MCPS የፕሮጀክት አፈጻጸም ዝርዝሮችን፣እና ጉድለቶችን ጭምር ማጋራት ወሳኝ እንደሆነ ሱፐርኢንቴንደንቱ ያምናሉ።

በዚህ ዓመት የ 2026 ዓ.ም የካፒታል በጀት ሲዘጋጅ የቻርለስ ኢ. ውድዋርድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የግንባታ ፕሮጀክት የሚያስፈልገውን የስቴት ባጀት ድጋፍ በቀረበበት ወቅት የተፈጠረውን ስህተት ለይተናል፣ይህም ለ 2026 በጀት ዓመት ከሚያስፈልገው ካፒታል በጀት ውስጥ $39.3 ሚሊዮን ዶላር የበጀት እጥረት እንደሚፈጠር ተገንዝበናል። ከ 2021 ጀምሮ፣ MCPS በተለያዩ የፕሮጀክት አፈጻፀም ደረጃዎች የምንዳ ክፍያዎችን እና የጨረታ ዋጋዎችን የተሳሳተ ስሌት ተደርጓል። ይህ ስህተት ሙሉ በሙሉ የ MCPS ነበር።

ይህን አይነት ስህተት መፈፀም እጅግ በጣም ተስፋ አስቆራጭ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም፤ የፕሮጀክቶቹ አፈጻፀም ወደፊት እንዲቀጥል ለማድረግ MCPS ይህንን ጉዳይ በግልፅ ማቅረብ እና ከባጀት አጋሮቻችን ጋር በንቃት መስራት አስፈላጊ እንደሆነ ሱፐርኢንቴንደንቱ ያምናሉ። ይህንን አስቸጋሪ ሁኔታ ለመቅረፍ አብረውን ለሚሰሩ የስቴት አጋሮቻችን ምስጋና እናቀርባለን። እና አስፈላጊ የሆኑ የት/ቤት ግንባታ ፕሮጀክቶችን እንዴት በተሻለ መልኩ ማጠናቀቅ እንደሚቻል ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል ጋር በመተባበር መሥራት እንፈልጋለን።

MCPS ከተጠናቀቁ ካፒታል ፕሮጀክቶች በመቀናነስ ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን የበጀት ክፍተት ለመዝጋት በንቃት እየሰራ ነው። እነዚህ የበጀት መቀናነስ ሥራዎች ለነዚያ ፕሮጀክቶች የታቀዱ ማሻሻያዎችን ወይም የመሰረተ ልማት ማሻሻያዎችን አይነኩም።

ሱፐርኢንቴንደንቱ ዋና ዋና የግንባታ ፕሮጀክቶችን ሙሉ በሙሉ እና በትክክለኛው መንገድ ሥራ ላይ ለማቆየት ከ CIP ባጀት መጠባበቂያ ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል። እነዚህ ፕሮጀክቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የመሰብሰቢያ አዳራሹን/ኦዲቶሪየሙን ጭምር የቻርለስ W. ውድዋርድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን እንደገና ለመክፈት ለግንባታ የሚያስፈልገው የገንዘብ ሚዛን ልዩነት።
- አዳራሹን//ኦዲቶሪየሙን፣ ስታዲየምን እና ሌሎች የመማሪያ ክፍሎችን ጨምሮ የአዲሱ ክራውን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ።
- በኖርዝዉድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህንፃ ምትክ ለስታዲየም እና ከቤት ውጭ ቦታዎች ግንባታ የሚሆን ገንዘብ።
- ኤ.ማሪዮ ሎደርማን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ወሳኝ የሆነውን የማሞቂያ፣ የአየር ማናፈሻ እና የአየር ማቀዝቀዣ መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ለማጠናቀቅ የሚያስፈልግ ገንዘብ።

የባጀት እጥረቱ የሚያስከትለውን አንዳንድ ተፅዕኖዎችን ብንቀንስም፣ MCPS እነዚህን የትምህርት ቤቶች ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ $21.6 ሚሊዮን ዶላር ከአካባቢ ድጋፍ እየጠየቀ ነው።

ሱፐርኢንቴንደንቱ እነዚህን ምክረሃሳቦች በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ሐሙስ፣ ኦክቶበር 24 በሚኖረው የስራ ክፍለ ጊዜ የበለጠ በዝርዝር ያቀርባሉ።

ግልጽነት፣ የውስጥ ቁጥጥር፣ እና የፋይናንስ ተጠያቂነትን ቅድሚያ ለመስጠት ቆርጠን ተነስተናል። ይህን በማድረግ ለተማሪዎቻችን በተቻለ መጠን ጥሩውን ትምህርት ለመስጠት ቁርጠኝነትን እንደምናሳይ ተስፋ እናደርጋለን።